# የምሁራን ደናቁርት ፭

ገ/ኢ. ጐርፉ

ክሕደት የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። ይሁንና፥ የተወለደበትን ኣገርና ሕዝብን ክዶ ለባዕድ የሚያጐበድድ፣ በሃገርም ውስጣዊ የፖለቲካ ጉዳይ የባዕድ እጅ ጣልቃ ገብቶ እንዲፈተፍት የሚፈቅድ፣ ኣልፎም የሚጋብዝና የሚጠራ ማንም ግላዊ ሰው ይሁን ድርጅት ለከሓዲነቱ ምን የሚያጠራጥር ነገር ሊኖር ይችላል?

በኰሎኒያል ወይም በቅኝ ኣገዛዝ ስር ተወልደው ላደጉ፣ ወይም በታሪካቸው የዚህ ጠባሳ ቅጽ ላለባቸው ይህ ዓይነቱን ኣሠራር መቀበል፣ ኣልፎም ትክክለኛ ነገር መስሎ ሊታያቸው ይችል ይሆናል። ኣንድ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ራሱን ኣቅንቶ ለሚሄድ ነፃ ሰውና በሃገሩ ታሪክ ለሚኮራ ሁሉ ግን፥ ይህ ጉድ እንዴት ብሎ ሊዋጥለት ይችላል?

የኣንድ ኣገር መንግሥት ተጠያቂነቱ ለገዛ ሕዝቡ እንጂ ለሌላ ኣገር ሕዝብና ለሌላ መንግሥት ከሆነ፣ የነፃነት ትርጉሙ ታድያ ምንድነው? ኢትዮጵያ በኣሜሪካ ለቆሙ ተጠባባቂዎች ‘ኣጥጋቢ ነው’ የሚሉት ዴሞክራሲያዊ ሂደት ካላሳየች በኣሜሪካ ምክር ቤቶች በወጣው ሕግ HR 2003 መሰረት ልዩ ተጽዕኖ እንዲደረግባት የሚለምን ሰው በባርነት የሚያምን፣ በቅኝ መገዛትን የሚለምን፣ ወራዳ ነው እንጂ ሌላ ምን ይባላል?

ከሓዲዎች በሃገራችን ላይ ሲነሱ ኣዲስ ነገር ኣይደለም። ከዚህ በፊትም በነ ነጋድራስ ኣፈ-ወርቅ ገብረኢየሱስ፣ በነ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳና በጥቂቶች ሌሎችም የነበረው የወራዶች ወግ ነው። ከጣልያን በኋላ ከሓዲዎቹ ተይዘው ከጠላት የተዋዋሉት ውል፣ ለሚሰጡት የስለላ ተግባርና ለሌላም ኣገልግሎቶች ጣልያን በስንት ሊሬ ሊከፍላቸው እንደ ተስማሙ ሰነዱ ተገኝቶ፣ በሕግ ፊት ቀርበው የሞት ቅጣትና የዕድሜ-ይፍታሕ እስራትም የተፈረደባቸው ነበሩ። ያኔ ወቅታዊ ሆኖ የተገጠመ ግጥምን ለማስታወስ፦

ዘርህ ከዘራቸው ኣይቀላቀል፣  
መልክህ ከመልካቸው ኣይመሳሰል፣  
እንደምን ተዋዋልክ እንዲህ ያለ ውል?      ይላል።

“በጅራቷ ብይዛት ዓይኗ ፍጥጥ ኣለ…” እንዲሉ፣ መልስ ኣጥተው ፍጥጥ ነው ያሉት። የዛሬዎቹ የምሁራን ደናቁርትም ከሓዲነታቸው ለነሱ ባይታያቸውም ለብዙ ሰው ግልጽ እየሆነ ነው። ለመሆኑ መልካቸው ከእነ Chris Smith (ዘመናዊው ኢያን ስሚዝ ነው?) ወይስ ከነ Donald Payne ጋር ቢተያይ ሓበሻን ነው ወይስ ኣሜሪካን የሚመስል?

“ኣይነጋ መስሏት… ከቋት ምንትንስ…” እንዲሉ፣ ከኣሜሪካ መደበቂያ ኣገኘን ብለው በሃገራችው ላይ የእጅ-ኣዙር ጥቃት ለማድረስ የሚጥሩ የዛሬዎቹ ኣጉል የምሁራን ደናቁርት ከሓዲዎች ወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፋረዳቸው ቀን እንደሚመጣ ኣይጠረጠርም። የከሐዲ ፍርድና ዕጣም ይደርስባቸዋል፣ ለውርደትም ይዳረጋሉ።

እስከዚያው ግን ሃገር ወዳድ ለሆነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የምንለው መልእክት ቢኖር፣ እኒህ ከሓዲዎችን እንዲያወግዛቸውና ‘ዓክ-እንትፍ’ ብሎ እንዲጠየፋቸው፣ ከዙርያውም እንዲያርቃቸው ነው። ሃገራቸውን የካዱ ከሓድያን ከሕብረሰቡ ራሳቸውን በራሳቸው ኣውጥተው፣ ፈቃዳቸውን ለባዕዳን ያስገዙ ናቸውና፤ ቄሱም፣ ሼኹም፣ ተራ ሰዉም ሁሉ ጭምር፤ ‘ውጉዝ እንደ ኣርዮስ’ ብሎ እንዲሸሻቸው ኣደራ እንላለን።